Amharic

Victorian Equal Opportunity
& Human Rights Commission

simply your rights

# በዘርና ሃይማኖት ስም ማጥፋት

## Racial and Religious Vilifcation

በቪክቶሪያ ውስጥ የአንድን ሰው ወይም ቡድን ዘር ወይም ሃይማኖት ምክንያት አድርጎ ስም ማጥፋት ህገ-ወጥነት ነው።

**ስም ማጥፋት ምን ማለት ነው?**

የዘር ወይም ሃይማኖት ስም ማጥፋት መጥፎ ፀባይ ሲሆን በሌላ ሰዎች ወይም ቡድን ዘር ወይም ሃይማኖት ላይ በመቃወም የጥላቻ ሽብር መንዛት፣ ከፍተኛ ንቀት፣ የመፀየፍ ወይም የማጀጃል ፀባይ ማሳየት ይሆናል። ስለ ስዎች ዘር ወይም ሃይማኖት የሆነ ነገር በመናገር ሌሎች ሰዎች እንዲጠሏቸው ማድረግ የዘር ወይም ሃይማኖት ስም ማጥፋት ይባላል።

ለምሳሌ በዘር ወይም ሃይማኖት ስም ማጥፋት የሚካተቱ:

- በአደባባይ የዘረኝነት ጥላቻ መጻፍና መሳል
- በአደባባይ የዘረኝነት ማስታወቂያ ማሳየት ወይም መለጠፍ
- በተለይ ስለ አንድ ሃይማኖት አናዳጅ አስተያየት በአደባባይ መስጠት ወይም በኢሜል በሰፊው ማሰራጨት
- በሕዝብ ስብሰባ ላይ የዘረኝነት ጥላቻ ንግግር ማድረግ
- አንድ ሰው ባለው ዘር ወይም ሃይማኖት የተነሳ መስደብና መምታት
- በዘረኝነት/ሃይማኖታዊ ተነሳስቶ ንብረት ማውደም ይሆናል

**ስም ማጥፋት ያልሆነ የትኛው ነው?**

በዘረኝነት የማይለወጥ አስተያየት፣ በትህትና አለመጥቀስ ወይም የዘረኝነት ቀልዶች እንደ ስም ማጥፋት ሆነው አይቆጠሩም።

ለሙዚቀኞች፣ ተዋናዮች፣ ጋዜጠኞች፣ አስተማሪዎችና ሳይንቲስቶች በጥሩ እምነት ከሥራቸው ጋር የተቀናጀ ከሆነ ይህንን ከህግ ውጭ ለመሥራት የሚደግፍ ለየት ያለ ግምት ይኖረዋል።

እንደ የኢሚግሬሽን፣ ሕብረ ባህላዊ፣ ስለ አቦርጅናል የመሬት መብቶች ጉዳይ ላይ አንስቶ መወያየት ስም ማጥፋት ሊባል አይችልም።

የሙዚቀኛ ሥራዎችን ማለት እንደ ባህላዊ ወይም የጎሳ ባህሪ ማንጸባረቅ ያሉትን በጽሁፍ ወይም በመድረክ ላይ ማቅረብ የስም ማጥፋት ሊባል አይችልም።

ስም ማጥፋት ማለት ስለምንናገረውና የምናደርገው ይሆናል። ማንኛውም ዓይነት ምርጫ ወይም እምነት እንዲኖረን ነጻ ስንሆን፣ ይህም ጥላቻን ወይም አንድን ብንበድልም ነገር ግን በራሳችን አስተሳሰብ ለሌሎች ጥላቻ የምንፈጥር ከሆነ ስም ማጥፋት ሊባል ይችላል።

**ስም ማጥፋት ህገ-ወጥ የሚሆነው መቼ ነው?**

በጣም መጥፎ ገጽታ ካለውና በአደባባይ ተነስቶ የዘርና ሃይማኖት ስም ማጥፋት ህገ-ወጥ ነው።

**እንዴት የቪክቶሪያ እኩልነት አስከባሪና የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ሊረዳ ይችላል?**

ማንኛውም ሰው በዘርና ሃይማኖት ላይ የስም ማጉደፍ ከደረሰበት ለኮሚሽኑ የቅሬታ ማመልከቻ ማስገባት ይቻላል። ይህ እንደ ሌሎች ዓይነት ቅሬታዎች ሳይሆን በራስዎ ለማስገባት ካልተመችዎ፣ ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት ማለት እንደ ለጎሳ ማህበረሰብዎ ቡድን ወይም ለሃይማኖት ቡድንዎ በመምረጥ እርስዎን በመወከል ያለዎትን ቅሬታ ለኮሚሽኑ ያቀርባል ማለት ነው።

በስም ማጥፋት ቅሬታ ላለባቸው ሰዎች መፍትሄ ያገኙ ዘንድ ሚስጢራዊ በሆነ፣ ነጻና በማያዳላ መልኩ የመፍትሄ አገልግሎት በማቅረብ እንረዳለን። ኮሚሽኑ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ፍ/ቤት አይደለም። ሰዎች ያላቸውን ቅሬታ መፍትሄ በጋራ ስምምነት ያገኝ ዘንድ እንረዳለን። አስተርጓሚ ካስፈለግዎ ለኮሚሽኑ ደውለው መጠየቅ ነው።

**ለምክር መስመር (03) 9281 7100**
**በነጻ ለመደወል (በገጠር ሆኖ ለሚደውል)**
**1800 134 142**
**መስማትና መናገር ለማይችል/TTY:**
**(03) 9281 7110**
**ኢሜል: complaints@veohrc.vic.gov.au**

በጥያቄ ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎት ይቀርባል።

**የክህደት ቃል**: ይህ ለመረጃ አቅርቦት መመሪያ ብቻ ተብሎ የቀረበ ነው። የህጋዊ የሆነን ምክር አይተካም።
**የርስዎ ብቻነት**: በቪክቶሪያ ነዋሪዎች የብቻነት ህጎች ላይ በእኩልነት መብት አስከባሪ የ1995 ዓ.ም አንቀጽ ህግ መሰረት የVEO&HRC ይከተላል። የብቻነት ፖሊሲያችን በድረገጽ፤ www.humanrightscommission.vic.gov.au/privacy ላይ ይቀርቧል ወይም ኮሚሽኑን ማነጋገር ይሆናል።
በቪክቶሪያ እኩልነት መብት አስጠባቂና በሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አድራሻ፡ 3/380 Lonsdale St, Melbourne, Victoria, 3000 ፈቃድ የወጣ የታተመ ጽሁፍ ነው።

April 2007